ያስተናግዳሉ:: እነዚህን መልሶ የማቋቋም ጉዳይ ሲነሳ የዘሬይቱ ካምቦዲያ ምስቅልቅሏ የወጣና የፈራረሰች አገር መሆኗን ማስታወስ ያስፈልጋል:: በመሆኑም ያለ ዓለም አቀፍ እርዳታ ምንም ማድረግ አይቻልም::

ብዙ የእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ይህንን ስለተገነዘቡ ካሁኑ ሥራቸውን በአገር አቀፍ ደረጃ ለማካሄድና በሃገር ግንባታው ጥረት ለማሳተፍ በያለበት መትከል ጀምረዋል:: ያለው ሁኔታ በየትም ታይቶ የማይታወቅ አስቸጋሪ ሁኔታ በመሆኑ የተባበሩት መንግሥታት ያወጡት ፕላን ካምቦዲያን ለተወሰነ ጊዜ በዓለምአቀፍ አስተዳደር ሥር እንድትቆይ የሚጠይቅ ፕላን ነው:: በዚህ መሠረት የተኩስ አቁሙን ስምምነት ከሥራ ላይ መዋሉ ለማረጋገጥ 10 ሺህ ወታደሮች ከውጭ እንዲመጡ፣ ይኸንኑ ያህል ባዕዳን ደግሞ በሃገሪቱ ተሰማርተው የአስተዳደሩን ሥራ እንዲሰሩ ተወስኗል::

እስከአሁን ድረስ እንደታየው ከሆነ ከሁሉም አወንታዊ ውጤት ያስገኘው ሳእስ ያካሄደቸው የመልሶ ማቋቋም ፕሮግራም ነው:: ይህም የሆነበት ምክንያት ለተወሰነ ደረጃም ቢሆን በኢኮኖሚው መስክ ለብራል የሆነ ፖሊሲ በመውጣቱና የሃገሪቱ መሪዎች ያወጡት የመልሶ ማቋቋም ፖሊሲ አንድ ወጥና ግትር ሳይሆን እንደሁኔታው እየታየና አስፈላጊው ማስተካከል እየተደረገ ከሥራ ላይ በመዋሉ ነው::

የሀገሪቱ መሪዎች በመልሶ ማቋቋም ፕሮግራማቸው ቅድሚያ የሚሰጡት በገጠር ተመልሰው ለመስማራት ለሚሹ ዜጎች ነው:: ሲመለሱም የተወሰነ የእርሻ መሣሪያ ተሰጥቶአቸው ሥራቸውን ወዲያውኑ እንዲጀምሩ ይደረጋል:: ይህም ሆኖ በገጠር ያለው የጤና አገልግሎት በጣም ወደ ኋላ የቀረ በመሆኑ በተለይ እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች በዚህ በኩል ቢሠማሩ ብዙ ሊያበረታቱ ይችላሉ ብዬ እገምታለሁ::

በአሁኑ ወቅት ከቬየትናም መሰደድ ከፖለቲካ ይልቅ በኢኮኖሚ ምክንያቶች የሚነሳሳ ነገር እየሆነ መጥቷል:: ይህ አዲስ ሁኔታ መንግሥታትንም ሆነ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን የዚህን የስደተኞች ጥያቄ ከሌላ አንጻር እንዲያዩት እያስገደዳቸው ነው::

በአንድ በኩል በአውሮጳና በተለይ በፈረንሣይ የሚካሄደው ክርክር አለ:: ሃብታም አገሮች ድህነትን እየሸሹ የሚመጡ ህዝቦችን ሁሉ መቀበል አይችሉም:: በሌላ በኩል ደግሞ ስደተኞች በሃገራቸው ያሉት ባለሥልጣኖች ሳይለወጡና በሚመጣው መንግሥት መጠነኛም ቢሆን እምነት ከሌላቸው ወደ ሃገር በገዛ ፈቃዳቸው አይመለሱም:: በዚህ የተነሳ፣ በተለይ እንደቬየትናም ያሉ ሃገሮች ነገሮች መለወጥ ያለባቸው "ከምንጩ" ነው የሚለውን ሃሳብ ብዙ ሰዎች እየተቀበሉት ነው:: ለዚህ ነው ዛሬ የቬየትናም መንግሥት በሚያደርገው ጥረት የዓለም አቀፍ እርዳታ በተለይ የአውሮጳ ኮሙኒቲ እርዳታ በሰፊው እንዲሰጠው ያስፈልጋል የሚለው ሀሳብ በመስፋፋት ላይ ያለው::

በሆንግ ኮንግ የሚገኙት የቬየትናም ስደተኞች ጉዳይ ለዚህ አዲስ ሁኔታ አንድ ምሣሌ ነው:: እነዚህ ስደተኞች ወደ ሃገራቸው ተመልሰው እንዲቋቋሙና ያለስጋት እንዲኖሩ በራሷ በቬየትናም ግዛት ውስጥ በዓለም አቀፍ ቁጥጥር ሥር የሚሆን የተመላሽ ስደተኞች ሠፈር የማቋቋም እቅድ አለ::

በዚህ ሁኔታ እንግዲህ የስደተኞችን ችግር ለመወጣት ብዙ ሰው የሚጠብቀው በዛው በሃገሩ ውስጥ መደረግ ያለባቸውን የአስተዳደር አደረጃጀት ለውጦችን ነው:: ከዚህ አንጻር ካቅርብ

ጊዜ ወዲህ በስደት ላይ ያሉ የቢየትናም ስደተኞች ኮሚኒቲያቸና በሃኖይ መንግሥት መካከል በመቋጠር ላይ ያሉት አወንታዊ ግንኙነቶች ተስፋ የሚሰጡ ናቸው። ይህ ሂደት ቀጥሎ ከታሰበው ግብ እንዲደርስ ቢየትናም አጠቃላይ የሆነ ተሃድሶ ያስፈልጋታል።ይህ ተሃድሶ በኢኮኖሚና በሶሻል መስኮች ብቻ መወሰን የለበትም። በካናዳ የሚገኙ እስከዚህም ድረስ ሃኖይን የማይቃወሙ የቢየትናም ተወላጆች "የእስተሳሰብ ተሃድሶ" የሚል ሃሳብ ሰንዝረዋል። እነዚህ ስደተኞች ከሁሉም በላይ ቀድሚያ ሰጥተው የሚጠይቁት በሃገራቸው የዜና ማሠራጫዎች ነጻነት እንዲያገኙ ነው።

የሆነ ሆኖ ከእንግዲህ ተስፋ ማድረግ የሚቻል ይመስለናል። እንደ ምንም ተጣጥር በኢንዶ ቻይና ቴክኒካዊ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካና ሰብዓዊ መፍትሄዎች መፍጠር የሚቻልበት ጊዜ የመጣ ይመስለናል። እንደዚህ ከሆነ ደግሞ ተጠቃሚዎች የኢንዶ ቻይና ሕዝቦች ብቻ ሳይሆኑ ከነሱም ለምዱ ሊማሩ የሚችሉት ሌሎች ህዝቦችም ይሆናሉ።

2. የአልጄሪያ ምሳሌ፣

በአቶ ታይበ ቡራህዋ
የባእድ ሠራተኞች የጤናና የማህበራዊ አገልግሎት
መ/ቤት ረዳት ኃላፊ
ቢትሪ /ፈረንሣይ/

በአልጄሪያ የቀደሞ ተዋጊያቸና የስደተኞች ጥያቄ ዛሬ ያለፈ ታሪክ ነው።ጦርነቱ ካለቀ 30 ዓመት ሊሆነው ነው። የዓለም አቀፍ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል። ይህም ሆኖ አንዳንድ ነገሮችን ማስታወስ ያስፈልጋል። ነጻነት ሊታወጅ ጥቂት ወራት ሲቀረው በአልጄሪያ ውስጥ የእርስ በርስ ጦርነት ተጀምሮ ነበር። በዚህ የእርስ በእርስ ጦርነት ሰቢያ አንዳንድ ተዋጊያች ለፈረንሣይ እስከመገዛት ደርሰው እንደነበር ማስታወስ ያስፈልጋል። እንደዚህም በመሆኑ ጦርነቱ ባለቀበት ጊዜ በራሱ በአርበኞቹ ሠፈር አሸናፊና ተሸናፊያች ነበሩ።

የአልጄሪያ ነጻ አውጭ ጦር በአሸናፊነት በመውጣቱ ዋናዎቹ ተሸናፊያች በደርዘን ሺህ የሚቆጠሩ በፈረንሣይ በኩል ሆነው የተዋጉት ሃርኪ የሚባሉት የአልጄሪያ ዜጎች ነበሩ። ከነጻነት በኋላ አንድ 12 ሺህ የሚሆኑ ሃርኩያችና ቤተሰቦቻቸው ወደ ፈረንሣይ ሄደዋል። አብዛኛው ግን እዛው አልጄሪያ ነው የቀረው። በእነዚህ ላይ ብዙ ግፍ ተፈጽሞአል። እንዲያውም አንዳንዴ በገፍ የተረሸኑበት ሁኔታ አለ። ግን ነጻ አውጭው ሠራዊት በተቻለው ሊያድናቸው ሞክሯል። ከዚያም በኋላ የአልጄሪያ ብሄራዊ ሠራዊት ሲቋቋም ብዙዎቹ እንደ ሲቪል ሠራተኞች ሆነው ተቀጥረዋል።

ታስረጡ የነበሩትም ሃርኪያች ቀስ በቀስ ተፈቱ። ፈረንሣይ አገር የሄዱት "ፈረንሣዮች አይደላቸሁም"ተባሉ። በግለሰብ ደረጃ የፈረንሣይ ዜግነት ለማግኘት እንዲያመለክቱ ተጠየቁ። አንዳንዶቹ በዚህ ሁኔታ በጣም በማዘናቸው የፈረንሣይን ትተው የአልጄሪያ ዜግነት እስከ መጠየቅ ደረሱ።

አሸናፊያቹስ? የነጻ አውጭው ሠራዊት አባላት በበረሃ በሚታገሉበት ጊዜ ብዙ ተሰቃይተዋል። በፈረንሳይ እስር ቤቶች ብዙ ግፍ የተፈጸመባቸውም ነበሩ። እነዚህ ተዋጊያች በአካላም ሆነ በሞራል በጣም የተጎዱ ሰዎች ነበሩ።

የነሱን ችግር ለመከታተልና ለመፍታት ራሱን የቻለ የቀድሞ ተዋጊያች ሚኒስቴር ተቋቋመ:: በዚህ ሚኒስቴር አማካኝነት ትንሽም ቢሆን ትምህርት የቀሰሙት ተዋጊያች እንደየችሎታቸው የሃላፊነት ቦታ ተሰጣቸው::

ሌሎች በተለይ የፖለቲካ ዝንባሌ የነበራቸው የገንባሩ ወይም የህዝባዊ ድርጅቶች ቋሚ ሠራተኞች ሆነው ተቀጠሩ:: አንዳንዶቹ ደግሞ በንግድና በሌላ በራሳቸው የአገልገሎት ሥራዎች ተሰማሩ::

በሌላ በኩል ግን ከገጠሩ ዓለም የመጡትና ምንም ትምህርት ያልነበራቸውን በዙህን መሰል የማቋቋሙ ተግባር ቀላል አልነበረም:: አንዳንዶቹ በሠራዊቱ ውስጥ የተላላኪነት ወይም የዘበኝነት ሥራ ተሰጣቸው:: ግን በጦርነቱ ጊዜ ከቷወቱ ከፍተኛ ሚና ጋር በማስተያየት ዛሬ እንደዚህ የተናቀ ሥራ ላይ መመደባቸውን እንደ ስደብ የቆጠሩ ብዙ ነበሩ:: በመጨረሻም ምንም ትምህርትና ሙያ ያልነበራቸው ቀደምሲልም በምንም ዓይነት የሥራ መደብ መስክ ተሰማርተው የማያውቁት ተዋጊያች በጡረታ መልክ የወር ገቢ ተቆረጠላቸው::

የስደተኞስ ጉዳይ? በ1954 እና 1956 ዓ.ም. የመውጣትና የመግባት ነጻነት ገና ያልተከለከለበት ወቅት ስለነበር ገንዘብ ያላቸው የገንባሩ ታጋዮች ለጆች ሞሮኮና ቱኒዚያ በስደት መልክ ሄዱ:: ከዚያ በኋላ ግን ጠረፉ ተዘጋ:: ተዋጊያችን ከህዝቡ ለመነጠል የፈረንሣይ ሠራዊት አንዳንድ አካባቢያችን "የተከለከሉ አካባቢያች" ብሎ ሰው እንዳይደርስባቸው አደረገ:: በነዚህ አካባቢያች ያሉ ሰዎች "መሰብሰቢያ ጣቢያ" በሚባሉ ሰፈሮች በግድ እንዲሰበሰቡ ተደረገ:: ከነዚህ ጣቢያዎች ለመውጣት የግድ የይለፍ ወረቀት አስፈላጊ ነበር:: በአጠቃላይ 4 ሚሊዮን ያህል ህዝብ ወይ በመሰብሰቢያ ጣብያዎች እንዲሰባሰብ ወይ ደግሞ ካለበት ተፈናቅሎ በትላልቅ ከተሞች ዙሪያ መጥቶ እንዲሰፍር ተገደደ:: ይህ በጊዜው ከነበረው የአልጀሪያ ህዝብ ግማሹ መሆኑ ነው::

ሃገሪቱ ነጻ ስትወጣ ሞሮኮና ቱኒዚያ የነበሩት ስደተኞች ወደ ሃገር እንዲመለሱ ተደርገው ፈረንሣዮች ለቀው በሄዱበት ቤቶች እንዲገቡ ተደረገ:: በመሰብሰቢያ ጣቢያ የነበሩትን ግን ወዲያውኑ ወደ መንደሮቻቸው እንዲመለሱ አልተፈቀደላቸውም:: አዲሱ መንግሥት የእነዚህ ሰዎች መበተን ወደ ደፈጣ ጦርነት እንዲገቡ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል ብሎ ስለፈራ ባሉበት እንዲቆዩ አደረገ:: ይህም በመሆኑ እነዚህ ዜጎች እንደቀድሞው አርሰው ወይም ከብት አርብተው ኑሮአቸውን ማደላደል አልቻሉም:: እንዲያውም ለህልውናቸው የአስተዳደሩ ጥገኞች ለመሆን ተገደዱ:: ቀስ በቀስ ግን እነዚህ ሰዎች ገጠራቸውን እየተው ወደ ከተሞች መፍለስ ወይም ደግሞ ሥራ ፍለጋ ወደ ፈረንሣይ አገር መሰደድ ጀመሩ::

ለ/ <u>የአልጀሪያ ምሣሌ</u>

በአቶ በርናር ሲገ

ሳይክትሪስት

አልጀሪያ ነጻ ስትወጣ የቀድሞ ተዋጊያችም ሆኑ ስደተኞች ሁኔታ ከሁለት አንጻር ተቀየረ:: በአንድ በኩል ከቀኝ ግዛት ተላቀው የአንድ ነጻ መንግሥት ዜጎች ሆኑ:: በሌላ በኩል ደግሞ እጅግ ከባድ የሆነ የኢኮኖሚና የሶሻል ለውጦች ለማካሄድ በጀመረች አገር ውስጥ ከጦርነት ወደ ሰላማዊ ሁኔታ ተሸጋገሩ::

ከነዚህም ሌላ አንድ ዋና ነገር ነበር:: ጦርነቱ በነዚህ ሰዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ሳይኮሎጂካል ቁስል አስከትሏል:: ብዙ ተዋጊዎች ከሀቡዕ ኑሮአቸው ይፋ ወጡ፣ ከእስር ቤት ተለቀቁ፣ በግድ ተቀጥረው ከነበረበት የፈረንሣይ ሠራዊት ተሰናበቱ:: በዚህ ላይ ደግሞ በጦርነቱ ጊዜ ሁለቱም ተዋጊ ወገኖች በየበኩላቸው ግፍ ይፈጽሙ ነበር:: በአልጀሪያ ዘመድ ያልሞተበት፣ ወይም በቶርቸር ያልተሰቃየበት፣ ሴቶች ያልታመጹበት፣ የትዳር መፈራረስ ያላጋጠመው ቤተሰብ በጣም ጥቂት ነው::

በተለይ የቀድሞ ተዋጊዎችን በሚመለከት ይህ ሳይኮሎጂካል ቁስል በጣም ከባድ ነበር:: እርግጥ ነው በህብረተሰቡ ውስጥ በጣም የተከበሩ ነበሩ እንዲያውም እነሱን ቦታ ቦታ ለማስያዝ አንድ ራሱን የቻለ ሚኒስቴር ተቋቁሞላቸው:: ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ ልክ በፈረንሣይ አገር እንደታየው በአልጀሪያም ስለጦርነቱ መወራት ቆመ:: ግን ደግሞ ከአንድ የጦርነት ወቅት ሲወጣ በተዋጊዎች ላይ የሚያስከትለውን ሳይኮሎጂካል ችግር ለመወጣት ስላለፈው ለምድ ማውራት መወያየት በጣም አስፈላጊ ነው:: በማህበራዊ ኑሮም ሆነ በሞያቸው በሚገባ ተሠማርተው እንዲሰሩ ከተፈለገ ያለፈውን ኑሮአቸውንና ታሪካቸውን በማውራት፣ ህብረተሰቡን በዚህ ጥያቄ ላይ ግንዛቤ እንዲያገኝ ለማድረግ ያላቸው ፍላጎት መታፈን የለበትም:: የቀድሞ ተዋጊዎችን ቁሳቁሳዊ ኑሮ ለማደላደል ብቻ ሳይሆን የመንፈስ ጥንቀታቸውንም ለማቃለል እርምጃዎች መውሰድ ያስፈልግ ነበር::

በዚህ መንፈሳዊ ጥንቀት በሚለው ጥያቄ ላይ በአልጀሪያ ሁለት ነገሮችን ለመታዘብ ችለናል::

1/ እንዲህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ጥንቀት ከሁሉ በላይ ያጠቃው ከገጠር የመጡትንና ባህላቸውን ትተው ሌላ የኑሮ ዘዴ መቀበል የሚቸግራቸውን ተዋጊዎች ነበር::

2/ የአልጀሪያን ሴቶች ተዋጊዎች የሚመለከት ነው:: እንደሚታወቀው ብዙ ሴቶች በአርበኝነቱ ትግል ተሳትፈዋል:: በጦርነቱ ጊዜ የተከበሩና የተወሰነም ቢሆን ነጻነት የነበራቸው ተዋጊዎች ነበሩ:: ጦርነቱ እንዳለቀ ተመልሰው "ወደ ማጀት" ገቡ:: በተዋጊነታቸው ዘመን ተጎናጽፈውት የነበረው መከበር እየቀዘቀዘ ሄደ:: ብዙ ሴቶች ይህንን ሁኔታ መቀበል አቃታቸው::

በመጨረሻም ስለ ወጣቶች ማውራት እፈልጋለሁ:: እንደሚታወቀው በጦርነቱ ጊዜ የተወሰነው የወጣት ክፍል ትምህርት ለመቀሰም ወደ ውጭ አገር ተልከው ነበር:: ወደ ነጻይቱ አልጀሪያ በተመለሱበት ወቅት የነበረባቸው አገሮች የተመቻቸ የኑሮ ሁኔታ የተዋሃዳቸው ሰዎች ነበሩ:: ችግር ባለበትና በመቋቋም ባለች አገር ውስጥ ለመኖርና ለመሥራት ብዙ ችግር አጋጠማቸው:: አንዳንዶች በሥራቸው ሁኔታም ሆነ በተቀረጠላቸው ደመወዝ ባለመደሰታቸው ብዙ ሳይቆዩ ወደ መጡበት ተመለሱ::

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የህጻናት ጉዳይ አለ:: በጦርነቱ ጊዜ የብዙ ህጻናት ወላጆች አልቀዋል:: የአልጀሪያ መንግሥት እነዚህን ለመርዳት ብዙ ጥረት አድርጓል:: በተለይ ለነሱ ብቻ በተቋቋሙ ተቋሞች እንዲማሩ አድርጓል:: በአጠቃላይ ጦርነት በተካሄደባቸው አገሮች ሁሉ እንደምንገነዘበው ጦርነቶች ቤተሰብን የመበተንና የማፍረስ ጠባይ አላቸው:: ይህንን ሁኔታ በሚገባ ለመቋቋም ጥረት ካልተደረገ መዘዙ ለሚቀጥለው ትውልድ ይተላለፋል::

## 3. የዚምባብዌ ምሣሌ፣

በወይዘር ዩዲት ተድ

ዚምባብዌ ለነጻነቷ በምትታገልበት ዘመን በጠሩ ትግል የተሳተፉት ሶስት ኃይሎች ነበሩ፡፡ እነሱም

1/ በሮበርት ሙጋቤ የሚመራው የዚምባብዌ አፍሪካዊ ብሔራዊ ህብረት /ዛኑ/ እና በዚሁ ድርጅት የሚመራው የዚምባብዌ አፍሪካዊ ብሔራዊ ነጻ አውጭ ሠራዊት /ዛንሳ/፣

2/ በጆሰዋ አንኮም የሚመራው የዚምባብዌ አፍሪካዊ ህዝባዊ ህብረት/ዛፑ/ እና በዚሁ ድርጅት የሚመራው የዚምባብዌ አፍሪካዊ ህዝባዊ ሠራዊት/ዚፕራ/፣

3/ የሮዴሽያ ግንባር የተባለው በኢያን ስሚዝ የሚመራውና የመንግሥቱን ሠራዊት የመንግሥቱን ሠራዊት ይቆጣጠር የነበረው የነጮች ግንባር ነው፡፡

በ1979 ዓ.ም. ሌላው ቀርቶ ደቡብ አፍሪካ እንኳን ለሮዴሽያ ግንባር ትሰጥ የነበረውን እርዳታ በማቆም የሮዴሽያ የነጮች መንግሥት ተደራድሮ ሥልጣን ለማስረከብ ተገደደ፡፡ በጦርነቱ የሚሳተፉት ወገኖች ሁሉ የሚሳተፉበት ጉባኤ በለንደን ተደረገ፡፡ ከዚህ በኋላ በአሜሪካንና በእንግሊዝ መንግሥታት እርዳታ አንድ ህገ መንግሥት ተረቆ ዚምባብዌ ነጻ የወጣች እለት አብር ታወጀ፡፡ በ1980 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ በጠቅላላው ህዝቡ የተሳተፈበት ምርጫ ተካሄደ የሮበርት ሙጋቤ ፓርቲ በአሸናፊነት ወጣ፡፡

የተኩስ አቁም ስምምነት በተፈረመበት በ1979 ዓ.ም.ና በሐምሌ 1981 ዓ.ም. መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ሁለቱ ነጻ አውጭ ሠራዊቶች /ማለትም ዛንሳና ዚፕራ/ በየሰፈሮቻቸው እንዲቆዩ ውሳኔ እንዲጠበቅ ተደረገ፡፡ በዚያን ጊዜ ታስቦ የነበረው ቀስ በቀስ የሥራ ፕሮግራም አውጥቶ ወታደሮቹ አምራች ኃይል የሚሆኑበትን ዘዴ ለመሻት ነበር፡፡ በልማት ሥራ የሚሠማሩ ወታደሮች ወይም "ሶልጀርስ ኢንሉይድ ኢን ኢኮኖሚክ ዲቨሎፕመንት" በተባለው ፕሮግራም መሠረት ቀደም ሲል የወታደር ማሰልጠና የነበሩትን ጣቢያዎች የእርሻ ማምረቻ ማዕከሎች ለማድረግ ተወሰነ፡፡ ግን ይህንን ፕሮግራም ወታደሮቹ በደስታ ቢቀበሉትም መንግሥት አልገፋበትም፡፡

ከዚህ ይልቅ ባለሥልጣናቱ የመረጡት በሠራዊቱ ውስጥ የነበሩትን 62,000 ወንዶችና 4,000 ሴቶች 400 የዚምባብዌ ዶላር እየከፈሉ ከሠራዊቱ ማሰናበትን ነበር፡፡ ውጤቱ በጣም አስከፊ ነበር፡፡ የተሰናበቱት የቀድሞ ወታደሮች ገንዘባቸውን ከጨረሱ በኋላ ሥራ ማግኘት ስላልቻሉ፣ እንደገና ወደ መጠለያ ሠፈሮች መጉረፍ ጀመሩ፡፡

ከዚህ ውድቀት በኋላ በሐምሌ 1981 ዓ.ም. ሌላ ፖሊሲ ወጣ፡፡ እንደገና 35 ሺህ ወታደሮች ከጦሩ ሲሰናበቱ ለሁለት ዓመት ያህል በወር 185 የዚምባብዌ ዶላር /ማለትም 300 የአሜሪካን ዶላር ገደማ/ ተቆረጠላቸው፡፡ በዚህ ገንዘብ አማካኝነት 5000 የሚሆኑት ተሰባስበው በተለያዩ መስኮችና/ማለትም በእርሻ፣ በሸቀጣሸቀጥ ንግድ፣ በትራንስፖርት፣ በማተሚያ ሥራ .../ የህብረት ሥራ ማህበራት አቋቋሙ፡፡

በመሠረቱ መንግሥት ይህንን የህብረት ሥራ ንቅናቄ ይደግፍ ነበር፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች በተጨማሪ የሚያስፈልጋቸውን ካፒታል ሊያቀርብላቸው አልቻለም፡፡ ስለሆነም ከነዚህ

በአሜሪካ 500 ሺህ በዶሚኒክ ሪፐብሊክ 400 ሺህ በኩባ 200 ሺህ በካናዳ 40 ሺህ የሄይቲ ዜጎች ነበሩ::

የዣን ክሎድ ዱቫሊየ መንግሥት መውደቅ አዲስ የነጻነት ዘመን ብቻ ሳይሆን ለሃገሪቱ ለማትና ብልጽግና በር ይከፍታል ተብሎ ተገመተ:: በዚህም የተነሳ ውጭ ይኖሩ የነበሩ የሄይቲ ዜጎች መመለስ ጀመሩ:: ከነዚህ ውስጥ በገዛ ፈቃዳቸው የተመለሱ ምሁራን፣ መካከለኛው መደብ ሰዎች፣ ገበሬዎች ነበሩ:: ከነዚህ ሌላ ደግሞ የፈሳጭ ቀራጩ አገዛዝ ሲወድቅ የስደተኛነት መብታቸውን ተገፈው ወደ ሃገራቸው በግድ እንዲመለሱ የተደረጉ አሉ::

እነዚህ ሰዎች ሲመለሱ በአንድ ዓይነት ሁኔታ አልተመለሱም:: ምሁራኖቹ የራሳቸው ፕሮጄክቶች ነበራቸው:: በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በዩኒቨርስቲ መምህርነት፣ በእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች እና በመንግሥት ሥራ ተሰማሩ:: በፈቃዳቸው ከተመለሱት ውስጥ ሌሎች ደግሞ በስደት ሳሉ ባጠራቀሙት ገንዘብ ትናንሽ ፕሮጀክቶች በማቋቋም ላይ አተኩሩ::

በግድ የተመለሱት ሁኔታ አስቸጋሪ ነበር:: ሃገር ለቀረት ዘመዶቻቸው ተስፋ ነበሩ:: ሃገር የግድ መመለሳቸው እንደ ውድቀትና ሃፍረት ተሰማቸው:: የኛ "የምእመናን ተራድኦ ድርጅት" ሥራ ያተኮረው እነዚህ ላይ ነው:: ሥራችንም በሶስት ይከፈላል::

1/ ተመላሾችን ተቀብሎ ማስተናገድ :: ተመላሹ ስለሚገኝበት ሁኔታ ውይይት ከተደረገ በኋላ እንደአስፈላጊነቱ እየታየ ወደ ትውልድ ክፍለ ሃገሩ እንዲሄድ የመጓጓዣ እርዳታ ይደረግለታል::

2/ ለተመላሹና ለቤተሰቡ የህክምና እርዳታ ይሰጣል::

3/ ተመላሹ ኑሮውን እንዲያደላድል መረዳት ነው::

በተለያዩ መስኮች የሸቀጣሸቀጥ ንግድ፣ የእጅ ሥራ፣ ከብት እርባታ፣ እርሻ ተመላሾች ፕሮጀክት ያቀርባሉ:: የሚቀርቡት ፕሮጀክቶች ከተጠኑ በኋላ በመጀመሪያ ከሚጠይቁት ወጭ 50% የሰጣል:: ከዚያ በኋላ የፕሮጀክቱ እርምጃ ተመርምሮ የቀረው 50% ደግሞ ይሰጣል::

ከ1986 ዓ.ም. ጀምሮ በዚህ መለክ ከረዳናቸው ፕሮጀክቶች 30% አልተሳኩም በተለይ በሸቀጣሸቀጥ ንግድ ላይ የመሠረቱት ፕሮጀክቶች ከሠሩ ይህም ያሆነበት ምክንያት በቂ ባለሙያ ባለመኖሩ፣ ሥራው እጅግ በፍጥነት በመራመዱ፣ የፖለቲካው ሁኔታ አለመረጋጋት፣ የሂሳብ ሥራና የንግድ አስተዳደር ትምህርት ያላቸው ተመላሾች አምበዛም በመሆናቸውና ገንዘብ የሚሰጡት ድርጅቶች አሠራራቸው ዳተኛ በመሆኑ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል::

ሌላም የተፈጠረ ችግር አለ:: በስደት ያልነበሩት የሄይቲ ዜጎች እነሱ ምንገዛም ያላገኙትን እርዳታ ተመላሾች ለምን እንደሚያገኙ ሊገባቸው ስላልቻለ በአጠቃላይ ፕሮጀክቶችን በክፉ ዓይን መመልከት ጀምሩ:: እኛም ራሳችንም ብንሆን በዚህ ጉዳይ መጠነኛችን አልቀረም:: ለምሣሌ የህክምና እርዳታው ጉዳይ ብዙ አከራክሮናል::ይህ. እርዳታ የሚደረገው በተለይ ለተመላሾች በመሆኑ "የቀረውስ ህዝብ?" የሚለው ጥያቄ ደግሞ በመነሳቱ "እስከ መቼ እንቀጥል" የሚለውን ነጥብ አስከማንሳት ደርሰናል::

በሌላ በኩል ደግሞ የምንደግፋቸውን ፕሮጀክቶች በምን መስፈርት እንምረጥ የሚልም ጥያቄ ነበር:: በዚህ አንጻር በተቻለን የምከርነው የምንደግፋቸውን ፕሮጀክቶች የግለሰቦችን ኑሮ ለማሻሻል የሚረዱ ብቻ ሳይሆኑ ሥራ በመፍጠር ለሃገሪቱ እድገት አስተዋጽኦ የሚያደርጉም እንዲሆ

ነበር፡፡ በተጨማሪም ለግለሰቦች ብቻ ሳይሆን ብዙ ሰዎች በጋራ ለሚያቋቁሟቸው ፕሮጀክቶች የተለየ ትኩረት ለመስጠት መክረናል፡፡

እንግዲህ ባጠቃለል በሀይቲ የተመላሾች ጉዳይ ገና የተሟላ መፍትሄ አላገኘም፡፡ መልሶ ማቋቋም የሚባለው ተግባር በጣም አስቸጋሪ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ችግር የተነሳ አንዳንድ ተመላሾች እንደገና አገር ለቀው ለመሄድ እስከ መሞከር ደርሰዋል፡፡